ወጣቶችና ፈተና

«ማንም በተፈተነ ጊዜ እግዚአብሔር ፈተነኝ አይበል እግዚአብሔር በክፉ አይፈትንምና እርሱ ራሱ ማንንም አይፈትንም። ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል።
ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ወልዳለች ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች።» የያዕቆብ መልእክት ፩፤ ፲፫-፲፭።

መፈተን ማለት ለኃጢአትና ለመጥፎ ተግባር ተሸንፎ መውደቅ ማለት ነው። ፈተና እራሱ ኃጢአት አይደለም። ኃጢአቱ ለፈተና ተሸንፎ መውደቁ ነው። በጣም የበቁትና ቅዱሳን የሆኑትም ለፈተና የተጋለጡ ናቸው። አንድ ቅዱስና ዐዋቂ የሆነ እንዲህ ይላል። «አዕዋፍ በራሳችን ላይ ቢያንጎበጡ ልንከለክላቸው አንችልም ነገር ግን ቤቶቻቸውን በጠጉራችን ውስጥ በራሳችን ላይ እንዳይሰሩ ልንከለክላቸው እንችላለን»።

የወጣትነት ጊዜ የምኞት ጊዜ ነው። ወጣቶች ከንቱ ምኞት ፈተና፤ ጦርነት ፤ ጥል አለባቸው። በዚህ ጊዜ ፈተናዎች ያጠቋቸዋል። እነዚያ የወጣትነት ፍላጎቶች ይገለጹባቸዋል። ትዕቢት ኩራት ትኩስነት ይታዩባቸዋል። መጥፎ ፍላጎቶችና ከንቱ ሐሳቦች የሚፈነዱበት ጊዜ ነው። ስለዚህ ጳውሎስ እንዲህ ይላል «ከብላቴንነት ፍትወት እራቅ» ጢሞ፪፡ ፳፪።

ፈተና ሲጀመር ቀላልና ጣፋጭ ሆኖ ነው። በመጀመሪያ ወደኛ ሲቀርብ መልኩን አሳምሮ ነው። ሲጀመር አኳኋኑና ሥራው በግልጽ አይታወቅም። ቀስ በቀስ በማስደሰት ሥጋን ያረካል ነፍስም በፍሥሐ ትቀበለዋለች። ከዚህ በኋላ ፈተና ወደ አሠቃቂና አሠቃይ ወህኒ ቤትነት ይለወጣል። ይህ በልዩ ልዩ ጥፋቶች ለተያዙ እውነት አይደለምን? ወጣቶች መጀመሪያ ሲወድቁ የመጀመሪያውን ጥፋት ሲያደርጉ ለፍትወታቸው ባሪያ እንደሚሆኑ ልብ አይሉም። የሚያዩት የፍትወትን መፈጸም ብቻ ነው። ይህ ምኞታቸው ወደ አጉል ልምድ ተለውጦ በመጨረሻ የፍትወት ተገዥ፣ የመጥፎ ፍላጎት እሥረኞች ያደርጋቸዋል።

የወጣቶች ፍላጎት አስፈሪ አውሬነት ይለውጣቸዋል። ወጣቶች አእምሮአቸውን ኅሊናቸውንና ሃይማኖትን አንቀበልም ማለት እውነትና ትክክለኛውን ይዞታ ባለመከተል እራሳቸውን እያጠፉ ሌሎችንም ወደ ማሳሳት በመስደድ እንዳያሰናክሏቸው ያስፈራል።

ፈተናዎችና ምንጮቻቸው

ፈተናዎች ከውስጣዊ ባሕርያችን ሊመጡብን ይችላሉ፤ ወይም ከጎን ከሚገኘው ከዓለም ፍትወት ይመጡብናል።
፩. ኃጢአት በውስጣችን ካለው ባሕርያችን ይመጣብናል በሕዋሳቱ ግን ያለው ሌላ የልቤን ሕግ ሰጠላ አያለሁ። «በሕዋሳቱ ወደ ዓለሙ ወደ ኃጢአት ሕግ ይማርከኛል» ሮሜ ፯፡ ፳፫። ኃጢአት በውስጣችን ሲያድር ይጐዳናል። ከአምላክ ርቀናል፤ ከፍላጎት፤ ከፈቃዱ፤ ከፀጋው፤ ከፍቅሩ ይወደናል። ክፋት ወደ ጥልቁ ልቦናችን ገብቶ ባሪያ አድርጎ ያጠፋናል። «የሰው ልብ ተንኰለኛከነገሩ ሁሉ ይልቅ እጅግ ክፉ ነው » ኤር ፲፯፡ ፱

፪. ፈተና ከዲያብሎስ ይመጣብናል። ነቅታችሁ ጠብቁ፣ ትጉም ሠይጣን ጠላታችሁ እንደሚጮህ አንበሳ ይዞራልና የሚውጠውን ሰው ሽቶ ሠይጣን እየተዋጋ በመታገል ፊት ለፊት ይቋቋመናል። ፈጣን ጠላት ስለሆነ ቀስ ብሎ በመቅረብ ይጠጋናል። ወደ ኃጢአት እስኪጥለን ድረስ ጓደኛችን ነው። ከወደቅንለት በኋላ ግን ጨካኝ ገራፊ ነው። ሼክስፒር ሠይጣን ጠንካራውን የጠቆረ ኃጢአት በፊታችን ሲያስቀምጥ የተሻለውን አስደሳች ሰማያዊ ልብስ ለብሶ ነው ብሏል።

ፈተና ከዓለም ፍትወት ይመጣብናል። በዓለም ያለው ሁለ የሥጋ መመኘት፤ የዓይን መመኘት የሰው ትምክህት ይህ ከአብ አይደደለም፣ ከዓለም እንጂ። ዓለም ክፉ አሳሳች በመሆኑ አደጋው ከፍ ያለ ነው። ዓለም እንደ ታላቅ ውቅያኖስ ማዕበል ሆኖ ሰውን በማሳሳት ያሰጥማል። ኃጢአት ሲቀርብና መጥፎ መልኩን ለመለወጥ በመሞከር ነው። በተገለጠ ጊዜ ግን ኅሊናችንን ያበላሻል።
የሰው ኅሊናው ዘወትር ወደ ክፋት አዘንባይ ነው ከበውን ያሉ ጥፋቶች የምናያቸው ትርኢቶችና የዓለም ማራኪዎች በመላ ልቦናችን እየገቡ ወደ ጥፋት ለመውደቅ ምክንያቶች ይሆኑብናል። የዓለም ፈተናዎች ብዙ በመሆናቸው ወጣቶችን አጥፊ ሆነው ይገኛሉ።
የወጣቶች ፈተናዎች የሚከተሉት ናቸው።

አልኮል

በክርስትና ትምህርት አልኮል የተከለከለ አይደለም። መጠጥ መጠጣትም ኃጢአትም ሆኖ እንደ ኃጢአት አይቆጠርም። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈው በመጀመሪያው መልእክቱ እንዲህ ይላል ደግሞ ውሀ ብቻ አትጠጣ ጥቂት ጠጅ ጠጣ እንጂ ስለሆድክ ስለደዌህም ብዛት ብሎታል። መስከርና መሳት ግን ኃጢአት ነው። ከመጠን በላይ መጠጣት ሰውን ስለሚያሳስትና ስለሚያበላሽ ይከለክላል።

እግዚአብሔር አለ፣ ወደ ጠጅ አትመልከት በቀላ ጊዜ መልኩ በብርሌ ባንፀባረቀ ጊዜ እየጣፈጠም ይገባልና። በኋላም ጠጅ ስለሆነ ወደ ክፋትና ወደ ዕብደት ያደርስሃል። ወጣቶችና አልኮል እሳትና ጭድ ናቸው። እንዲሁም ዋይታ ለማን ነው? ሐዘን ለማን ነው ፀብ ለማን ነው? ጩኸት ያለ ምክንያት መቁሰል ለማን ነው? የዓይን ቅላት ለማን ነው? ጠጅ በመጠጣት ለሚዘገዩ አይደለምን የወይንን ጠጅ ይፈትኑ ዘንድ ለሚሰበሰቡ ምሳ ዐዋቂዎች ሐኪሞች የፖለቲካና የሃይማኖት ሰዎች የተወሰነ ጥፋት ማለት በገንዘብ ማባከን ሞራል በማሳጣት፣ በቤተሰብ መሐከል በማቁሰል ጉበትን፣ ሳንባን፣ ኩላሊትን በማሳመም በመጨረሻም ያሳብዳል ይላሉ። ስካር የእግዚአብሔርን መልክ ያበላሻል፣ ሰብአዊነትን ያቃልላል፣ የአንጎልን ንቃት ያደድባል፣ ክብርን ይደመስሳል፤ ጎሊናን ይጐድላል። መስከር ነውር ነው። በጦርነት ላይ ከሚያልቀው በብርሌ የሚያልቀው ይበልጣል።

በአንድ አገር የተደረገ አንድ ጉባኤ ስለመጠጥ ጎጅነት ቀጥሎ ያሉትን ውሳኔዎች ሰጥቷል።

ሀ/ የሚያሰክር መጠጥ ምግብ እንዳይዳቀቅ ያውካል።
ለ/ የእህልን ፍላጎት ይከለክላል።
ሐ/ አያፋፋም።
መ/ አያሞቅም። ምናልባት እንዲያውም ሰውነትን እያቀዘቀዘ ወደ ሞት ያደርሳል።
ሠ/ ሰውነት በሽታን እንዳይቃወም በማድከም አካልን ለሕመም እንዲጋለጥ ያደርጋል።
ረ/ ብርታትን አይሰጥም። ጠባይን ያበላሻል።
ሰ/ የአእምሮን የአካልን ኃይል ያጠፋል።
ሸ/ በማደግ ላይ ላሉት መርዝ ይሆንባቸዋል።
ቀ/ ዕብደት ከአልኮል ይመጣል።

አዋቂዎች አልኮል ከኦፒየም የበለጠ ጎጅ ለመሆኑ ያረጋግጣሉ።
ከመጠን ያለፈ አልኮል ኃይላችንን፣ ሥራችንን፣ ገንዘባችንን፣ ወዳጆቻችንን፣ ቤተሰባችንን፣ በራስ መተማመንን ፣ ጤናችንን ፣ ሕይወትችንን ያሳጣናል። አልኮል አስደሳች ነው የሚባለው አነጋገር ሐሰት ነው። ያከሥራል። ሙልጭ ያወጣል። መጠጥ መርዝ እንጂ ምግብ አይደለም፤ ገዳይ እንጂ አዳኝ አይደለም። አሳዛኝ እንጂ አስደሳች አይደለም፤ ጎጂ እንጂ ጠቃሚ አይደለም። አካልን ይጐዳል፣ አቋምን ያበላሻል፣ የወንድነትን ክብር ያሳጣል፣ የሃይማኖትን ክብር ያጠፋል። ለጠጪ በሽተኛ ሰው መድኃኒት ሰጥቶ ማከም መድኃኒት ማባከን ነው።

ሼክስፒር ስለመጠጥ ሲናገር እንዲህ አለ። «የማትታወቀው የአልኮል መንፈስ ሆይ ስምህ በእኛ ዘንድ ያልታወቀ ቢሆን ኑሮ የዲያብሎስ መንፈስ ብለን በጠራንህ ነበር። ጠጅ ከሚጠጡ ጋር አትቀመጥ ሥጋቸውን ከሚያጠፉ ጋር ምሳሌ ሰዎች አልኮልን ለምን ይጠጣሉ? ልማድ እየሆነባቸው ይጠጣሉ። የማይጠጡትን ደረቆችና ያልሠለጠኑ ይሏቸዋል።»

በልምድ ምክንያት ይጠጣሉ፣ ሌላው እንዲጠጣ ለማበረታታት ኃይልም ይሰጣል ይላሉ። ለተውሳክና ለነቀርሳ በሽታ መድኃኒት ነው ይላሉ። ይህ ሞኝነት ነው። አልኮል አካልንና አእምሮን ያነቃቃል ብለው የሚያምኑ አሉ። ይህ ልክ አይደለም። ያደክማል እንቅልፍ እንቅልፍ እያሰኝ ያስተኛል። አልኮል ለጊዜው ልብ በኃይል እንዲመታ ሰውነት እንዲንቀሳቀስ ሲያደርግ ይህንን ሥራ የሚቆጣጠረውን ነርቭ ሲገድል ነው።

አልኮል አንጐልንና ነርቭን ይጐዳል። ሰው ራሱን እንዳይቃወም ያደነዝዘዋል። ጠባዩን ያሳጠዋል።
ጠጭ ሥራ ያሳስታል፣ መቀመጥ አይችልም እራሱን አይቃወምም፣ መልካም ሰው ነኝ ይላል ሰውነቱን ገንዘቡን አይጠብቅም፣ ይጠብቀና የነበረውን ሕግ የሽራል ይቃወማል ሞራሉን ያጣል፣ ቀጠሮ አያከብርም፣ ኃላፊነትን ይረሳል፣ ለፍላፊ ይሆናል፣ ጎሊናውን ይስታል አንደቡቱን አይገታም፣ የሚወደውንና የማይወደውን በጩኸት ይናገራል፣ ለጥል የተዘጋጀ ነው። ባሕርዩን ለመቆጣጠር አይችልም፣ ቶሎ ይቆጣል፣ ተቆጥቶ ወዲያው ይመለሳል ዕቃ ያጠፋል፣ ለአደጋ የተዘጋጀ ነው። ለማንኛውም ነገር መልስ አልኮል የሥራንና የማሰብን ኃይል ያሳንሳል፣ በባዶ ሆድ ሲጠጣ በጣም የከፋ ይሆናል። ወይም ሦሥት ብርጭቆ አልኮል የሚጠጡ ሰዎች በብዛት እንደሚሞቱ ታውቋል።

አልኮል ዕድሜን ይቀንሳል ለበሽታ ያጋልጣል፣ ጠጭ ከበሽታው ቶሎ አይድንም የነርቭ መቃወስና የእብጠት በሽታ በአልኮል ምክንያት ይመጣል።
ብዙ የመኪና አደጋ የሚደርሰው በአልኮል ጠጭዎች ነው። የጠጣ አደጋን አይፈራም፣አረማመዱን አይገታም፣ አደጋን አይከለክልም። ጠጭ ሥራ ሊያገኝ አይችልም፣ የሚጠጣ ከሥራ ይወገዳል፣ ከተወገደም በኋላ ችግሩን ለመርሳት ወደ መጠጥ ቤት ይሄዳል።

ደመወዘተኞች ከምግባቸው፣ ከልብሳቸው፣ ከመኖሪያቸው ላይ እየቀነሱ ለአልኮል ያወጣሉ። አልኮል በድሆች ዘንድ የበሽታና የድህነት ምክንያት ነው።
አልኮል ከሞራል ውጭ ያደርጋል። ጠጭ የሚያደርገውን ሁሉ በነፃ ያደርጋቸዋል ፈተናን ለመቃወም ያቅተዋል።

ቁማር

ቁማር እራሱ ኃጢአት አይደለም ግን የኃጢአት መንሥኤ ይሆናል። ቁማር ተጫዋቾች ሌሎችን ሰዎች ሚስቶቻቸውንና ልጆቻቸውን ለአደጋ ያጋልጣሉ። ለቤተሰቡም የጥፋት ምክንያት ነው። አልኮል ፍትወትን ሲፈጥር ቁማር በተጨዋቾች ላይ ስስትን ይፈጥራል። ገንዘቡን መብላትና መሰብሰብ ወደ ቁማር ጨዋታ ከሚገፋፉት ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ነው። ሀብትን ማማኛ ብዙ የከበሩ መንገዶች አሉ።

ብዙዎች ሰነፎች የተለያየ የገንዘብ ማግኛ ዘዴዎች አላቸው። እነዚህንም በማታለል፣ በመቀማት፣ በመዝረፍ፣ በመስረቅና በቁማር ናቸው። ይህ ሁሉ ስርቆት ነው። አትስረቅ የሚለው ስምንተኛው ትእዛዝ፣ የሞራል ሕግ ይከለክላል። በዚህ አኳኋን ቁማር ስርቆት ነው። ቁማርን አንድ ሰው ቢያቋቁመው መንግሥትም ቢያደራጀው ወይም ድርጅት ቢያቋያሂደው ለማኅበራዊ ኑሮ ወይም ለቤተክርስቲያን ጠቃሚ ሆኖ ቢገኝም የሞራል ሕግ ስለሚቃወመው አይደገፍም።

መጥፎ መሆኑን እየተገነዘቡ ጨዋታው ይገባል እያለ የሚተቹ አሉ። ቁማርን በሚጫወቱት ሰዎች መካከል ወንድምነትን መከባበርን ይርቃል እራስን ብቻ ወዳድ ያደርጋል ያሰስታል። ቁማርን የሚያንቀሳቅሱ በርካሽና በቀላሉ ለማትረፍ የሚፈልጉ ናቸው። ቁማር ክፋትን የተከተለ ነው። ማኅበርን አፍራሽና ኃጢአትን ፈጣሪ ነው። ቤትንና ቤተሰብን ያናውጣል። ጻድቁን ያሠቃያል፣ የድኅነትን ጐዳና ለደኅንነት ያሳምራል። ጊዜን ያጠፋል ለሚስትና ለልጆች የሚሆነውን ቅርስ ያስጠፋል። ቁማር ክብርንና ጤናን ይጐዳል። ዕረፍትንና ደስታን ይቀንሳል። ገንዘብ የእግዚአብሔር ስለሆነ ለነፍሳችንና ለሥጋችን መጠቀማያ የተሰጠ ነው። ጋብቻን መደገፊያ ልጆችን ማሳደጊያ፣ መታከሚያ፣ ደሆችን መርጃና በጎ ማድረጊያ ነው። ለቁማር ካጠፋነው የቤታችንን ፣ የማኅበሩን፣ የሃይማኖትን ቅዱስ ግዴታ በመርሳት እንደመበተንና ገደል እንደ መወርወር ነው። ብዙዎቹ ባለፈው ሕይወታቸው አየተጸጸቱ ባልጠጣሁ ቁማር ባልተጫወትሁ ይላሉ።

ሲጋራ ማጨስ

ታላቁ አዋቂና ሐኪም ስለ ሲጋራ ብዙ ከማንበብና ከብዙ ጥናት በኋላ ቀጥሎ ያለውን ይጽፋል።

ሀ/ የሚያጨሱትን ሰዎች ነርቭ የሚበጠብጥ ኒኮቲን የሚባል መርዝ አለ።

ለ/ ጥርስን ያጣምማል ከንፈርን ያቃጥላል በልብ በዓይን በሆድ ዕቃ በኩላሊቶች ላይ ከፍ ያለ እክልን ይፈጥራል።

ሐ/ አካል እንዳያድግ በመካከል የተሟላ እንዳይሆን ያደርገዋል።

መ/ የሚያጨሱትን ሰዎች ዓየሩን በጢስ በመሙላታቸው የሌሎችን መብት አልጠበቁም ነገር ግን ብዙዎች በጥፋት ልጆቻቸውንና ቤታቸውን ይማርካሉ።

ዓለም በመጠጥና በጢስ ተውጧል። አእምሮው ያልደከመ፣ አጽሙ ያልሰለለ ትውልድ ይፈለጋል። መልካም ልምድና ቆራጥ ኃይል ያለው ትውልድ ይሻል። የዛሬ ትውልድ ግን በሲጋራ መርዝ ተውጧል። ቶማስ ኤድሰን እንዲህ ይላል ሲጋራ ነርቭን ይጐዳል፣ የአንጐልን ሴሎች ያጠፋል።

ማመንዘር

በክርስትና ትምህርት ሕጋዊ በሆነ መልክ ሥጋዊ ፈቃድን መፈጸም ኃጢአት አይደለም። ልቅ ፍትወትን መፈፀም ግን ኃጢአት ነው። ኃጢአት የሚባለው አታመንዝር የሚለውን ትእዛዝ መጣስና የሰው ሥጋዊ ፍላጎትን ባደረገ ቁጥር በየሥፍራው በስድነት ልጆችን በመውለድ ዓለምን በፍጥነት በሰው ዘር መልቶ ሕግንና ሥርዓትን ሲያበላሽ ነው። ይህ አእምሮ የማይደግፈው ወይም የእውነት ሕግ የማይስማማበት የክርስትናን ታላቅ ስምም የሚያጠፋ ነው። ክርስቲያን ሁሉ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነው። «ዝሙት ርኩሰት ሁሉ ስስትም ከቶ አይሰማባችሁ ለቅዱሳን እንደሚገባ» ኤፌ፭፡፫።

ዝሙት የንጹሕ ነፍስ ፈተና ነው። የክርስቶስን አካል ማርከስ ነው። ቅዱስ መንፈስን ማቃለል ነው። ዝሙት ነፍስን ይገድላል። መልካም ስሜትን ያበላሻል። ክርስትና ዝሙት መሥራትን ብቻ ሳይሆን ከፋ ማሰብ መመኘት መመልከት ሁሉ ወደ ኃጢአት ተቆጥሮ ይህን የፈጸመ በሥራ እንዳደረገ ተናግሯል። ክርስቶስ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ፈጽሞ በልቡ አመነዘረባት ብሏል። ወደ ሴት በፍትወት መመልከት የመውደቂያ ምልክት ነው። ሔዋን ስላየች ወደቀች። ዳዊት ከመመልከት የተነሣ ወደቀ። ፈተና በየመንገድ ላይ በቤታችን ውስጥ በሥራ ሥፍራችን በአንዳንድ መጽሐፍ ውስጥ እንዲሁም በሲኒማ ቤቶች ይገጥመናል። አደናግረው እንዳይጥሉን መጠንቀቅ ይገባናል። አስተሳሰባችን ንጹሕ ይሁን መጥፎ ሐሰብ መውደቂያ ነው። ከንቱ ሐሳብ እንደሚያልፍ እንግዳ በደጃፍ ያልፋል፣ ቀጥሎ ይገባል፤ ከዚያም የማጥመድ ሥልጣኑን ይዘረጋል። መጥፎ ነገርን ሳናቋርጥ እናስባለን ከንቱ ወሬ መጥፎ ሥፍራ ክፉ ሐሳብ ያመጣብናል። ሥራ ሳንፈታ ወደ ጥፋት አናዘነብላለን።

ወጣቶች ሊታገሉ የሚገባቸው መጀመሪያ ላይ ነው። መመልከተን፣ መሰማትን መጥፎ ሃሳብን ወዲያዉኑ መቃወም ይኖርባቸዋል። ያስደስተናል የምንለዉ ጥፋትን ሳንመለከት ነዉ። እሾኽን ተክለን ወይንን አናመርትም ። «ለሥጋዉ የዘራ ከሥጋዉ ጥፋትን ያጭዳል» ገላትያ ፮ ፡ ፰ በመጀመሪያ እንስቅ ይሆናል በመጨረሻ ግን እንባ ሳይሆን ደም እናለቅሳለን።

ዝሙት ኀሊናን ይበጠብጣል፣ ክብርን ይቀንሳል፣ ነፍስንና ሥጋን ይጎዳል፣ ክርስቲያናዊ ጠባይን ያበላሻል፣ ከእግዚአብሔር አንድነት ይለያል፣ ሞት ያስከትላል።

የዝሙት ኃጢአት በአካል፣ በአንጎልና በነፍስ ላይ አደጋንና ጉዳትን ያመጣል።

ሀ/ የዝሙት ኃጢአት ነፍስን ይጎዳል። በዝሙት ኑሮ የሚኖሩ ወጣቶች በነፍሳቸዉ የታመሙ ይሆናሉ። ኀሊናቸዉ ይበጠበጣል ይቃወሳል ውሰጣቸዉ ይሰቃያል። ይህ ኃጢአት ከእግዚአብሄር ያርቀናል። መልካም አምልኮን ሃይማኖትን ያስጥላል። ኀሊናን የወደቀ ያደርገዋል ፈቃድን አድክሞ ባሪያ ያደርጋል። «ኃጢአት የሚያደርግ ሁሉ እርሱ የኃጢያት ባሪያ ነዉ።» ዮሐ. ፰ ፴፬

ለ/ የዝሙት ኃጢአት ሞራልን ይጎዳል። በዚህ የተያዙ ወጣቶች ክብራቸዉን፣ ታላቅነታቸዉን፣ ጀግንነታቸዉን፣ ድፍረታቸዉን ያጣሉ። ጽናታቸዉን ያናዉጣሉ።ታማኝነታቸውን ያሳጣቸዋል። ምክንያቱም ትክክለኛው መንፈሳቸው በውሰጣቸው የደከመ ሰለሚሆን ነው ከኀደኞቻቸውና ከዘመዶቻቸው ያርቃቸዋል። ሕግ ነፍሰ ገዳዩን ከሰዎች መካከል ይለያል ። ነገር ግን ሰካራሙንና አመንዝራውን ለመለየት እንደምን ይቻላል?

ሰዎች ዝሙትን አሰፈሪ አድርገው ይመለከቱታል፣ ክፉ ባርነት ነው ይላሉ።ከሞራል ህግ ውጭ ሆኖ ራሱን የማያከብረውን ሰው ሌሎች እንደምን ሊያከብሩት ይችላል? አንዳንድ ድሆች ራሳቸውን በመግታትና በመጠበቅ ክብርንና ምሰጋናን ሲያገኙ ሀብታሞች ባለማዕረጎች የምግባር ድሆች ሆነው እንሰሳዊ ባህሪያቸው ሲያሸንፋቸው ይታያሉ ። «ትዕግሥተኛ ሰው ከብርቱ ሰው ይሻላል በመንፈሱም የሚገዛ ከተማ ከሚወሰዱ ይበልጣል።» ምሳ ፲፮ ፡ ፴፪።

ሐ/ ዝሙት አካልንና አንጎልን ይጐዳል። ሐኪሞች መርምረዉ ባገኙት ዕዉቀት መሠረት ማመንዘር ዝሙት ፈጻሚያንን በጠነከረና አደገኛ በሆነ በሽታ ሳይመታ እንደማይተዉ ይናገራሉ። ስንት ወጣቶች ናቸዉ በቂጥኝ፣ በጨብጥና በሌላ በሽታ የተመረዙ? በሽታዉ አጥንታቸዉን ያነቅዘዋል፣ ችሎታቸዉን ይቀንሰዋል ደማቸዉን ያቆሸሸዋል። ከበሽታዉ አይላቀቁም። በሽታቸዉ ቢደበቅም በሦስተኛዉና በአራተኛ ዉ ትውልድ ይገለጣል። ወደ ልጅ ልጅ ይዛወራል። ወጣቶች በልጆቻቸዉና በሚሰቶቻቸዉ ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት ቢገነዘቡ ከኃጢአታቸዉ በተወገዱ ነበር። ዝሙት አካልን ያደክማል፣ አንጎልን ያዞራል፣ የቤተሰብን ደሰታ ያሳጣል። ገንዘብን ያጠፋል፣ ክብርን ይቀንሳል፣ ወፈፍተኛ ያደረጋል።

መ/ ዝሙት ጉዳቱ በዚህ ዓለም ብቻ አይደለም ዘለዓለማዊ ጉዳትን ያመጣል። ጉዳቱ በአካል፣ በአንጎል፣ በክብር፣ በገንዘብ ላይ ብቻ አይደለም። «አመንዝሮችንና ጋለሞቶችን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል።» ዕብ ፲፫ ፡ ፬ ። ዘለዓለማዊውን ደሰታን በኃላፊዉ ደስታና በጊዜያዊዉ ፍትወት መለወጥ አይገባም።

<u>ክህደት</u>

የወጣቶች ፈተናዎች ብዙ ናቸው። ሥጋዊ ፍላጎት ያስራቸዋል፣ ስስት ያጠቃቸዋል፣ አጥፊ ልማዶች ይዟቸዋል። ውሳጣቸዉ ባዶ ይሆናል። አሳሳች ታሪክን ብቻ በማንበብ ከንቱ የሆነውን ብቻ ይመርጣሉ። ርቀው በመጥፋት ሁሉን እየነቀፋ የእግዚአብሔርን ቤት ቃሉን በማቃለል ሃይማኖትን ችላ ብለዋል። በአሁኑ ጊዜ በወጣቶች ዘንድ መንፈሳዊው ይዞታና መልካሙ ጠባያቸዉ ጨርሶ እንዳይጠፋ ያሳስባል። በየቦታዉ ወጣቶች በክህደት እየተያዙ ይታያሉ። በብዙዎቹ ላይ «ኃጢአትን እንደ ዉሀ ይጠጣሉ።» ኢዮብ ፲፭ ፡ ፲፮ የሚለው እንዳይፈጸም ያሰጋል። ክህደት በልቦናቸዉ ወይም በአእምሮአቸዉ የጸደቀ ይመስላል። በሳይንስ የሚፎክሩት ሳይንስን ባለመገንዘብ ነው እንጂ ሳይንስ የእግዚአብሔርን አለመኖር አልተናገረም። አንዳንዶቹ በእግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስና በነፍሳቸው ተጠራጥረዋል። እንደ እንሰሳት ኖረው እንዲሞቱ የፈለጉ ይመሰላሉ።

በወጣቶች ውሰጥ ተሸፍና ያለች ዉድ ዕቃ አለች። እሷም ዉዲት ነፍስ ነች። ነፍስ ሕይወታችንን በእግዚአብሔር ላይ እንድንመሠርት የምታሰማን ድምፅ ነች። በመንፈሳችን እንድንጽናና በዉሰጣችን ሰላም እንዲኖር ትጠይቃለች። ነገር ግን ሥጋ በፍላጎቱ በፍትወቱ የክህደትን ሐሳብ እያመጣ ጥርጣሬን ፈጥሮ እዉነትንና ደጉን መሠረት ሊያፈርስ ይጥራል። ይህ ሁሉ ፍላጎትን ለማርካት ነዉ።

ወጣቶች በወጣትነት ዘመን ላይ ሲደርሱ እምነትን መንቀፍ ይጀምራሉ። ይህ የሚያመለክተዉ የተደበቀ ኃጢአት እንዳደረባቸዉ ነዉ። ዳዊት «ሰነፍ በልቡ እግዚአብሔር የለም ይላል።» መዝ ፲፬ ፡ ፩ ። የሥጋዊውን መንገድ በመከተል የክሕደትን ሐሳብ ይዘዋል። በዕውር ኩራት በመያዝ ኃይላቸዉን ያመልካሉ። ነገር ግን ይህ የክፋት ማዕበል ሆኖ ያጠፋቸዋልና የእምነትን ቁርጠኝነት መመልከት ያሰፈልጋቸዋል። ሥጋዊ ደሰታና ፍትወት ንቀትንና ጥፋትን ብቻ እንዳያስከትልብን ያሰጋል።

ወጣቶች ወደ እግዚአብሔር ሊመለሱ ግድ ነዉ። በልቦናቸው ያመኑ ይህ ሲሆን የጸጥታን ሕይወት ይኖራሉ። የድል ሕይወት የንጽሕናና የታመነን ኑሮ ያያሉ። ሶሎሞን እንዲህ ይላል «አንተ ጎልማሳ በሕፃንነትህ ደስ ይበልህ።» መክ ፲፩ ፡ ፱